ዓባይ ባንክ
Abay Bank

ዓመታዊ ሪፖርት

2013 ዓ.ም

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2021
ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት

ዓባይ

ዓባይ ባንክ
Abay Bank

በተላከልዎት ቅጽበት ገንዘብዎን በቀጥታ ይቀበሉ !

RECEIVE YOUR MONEY ON TIME ...!

ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ
Abay - The Trustworthy Bank
Tel +251 11 515 8961, +251 11 554 9735 E-mail: info@abaybank.com.et
Ziquala Complex, Jomo Kenyatta Avenue, ADDIS ABABA, ETHIOPIA
web: www.abaybank.com.et

/abaybanksharecompany

/AbayBank

@AbayBank

/abaybanksharecompany

/In/abaybank

ማውጫ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር መልዕክት 7

የዋና ስራ አስፈጻሚ መልዕክት 8

የዓበይት ክንውኖች አጭር መግለጫ 9

ክፍል 1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት 14

1.1. ኦፕሬሽናል ክንውኖች 14

1.2. ገንዘብ-ነክ ክንውኖች 16

1.3 ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ክንውኖች 17

1.4 ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች 18

ክፍል 2: የኦዲተሮች ሪፖርት 21

2.1 ትርፍ ወይም ኪሳራ እና ሌሎች አጠቃላይ ገቢዎች መግለጫ 23

2.2 ሃብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫ 24

2.3 በአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል ላይ የታየውን ለውጥ የሚያሳይ መግለጫ 25

2.4 የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ 26

ራዕይ

የላቀ ባንክ መሆን!

ተልዕኮ

የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በማቀናጀት የተሟላ የባንክ አገልግሎት በመስጠት የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ማድረግ፡፡

የባንኩ ዕሴቶች

- የደንበኞችን እርካታ ማረጋገጥ፣
- ታማኝነት፣
- በጋራ መሥራት፣
- ዘመናዊ አሠራርን ማስረፅ፣
- የሠራተኞችን እርካታ ማረጋገጥ፣
- ማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት

ፕ/ር አምሀየ ስለሽ
የቦርዱ ሰብሳቢ

ዋሪት አማተብያ ታደሰ
የቦርድ ፀሐፊ

አቶ ጌታሁን አትዓለሁ
የቦርድ አባል

አቶ ሳኒቲ ዓሊ
የቦርድ አባል

አቶ ማሩጥ የሰውምክነት
የቦርድ አባል

አቶ ሙሳቴ ቢጋ
የቦርድ አባል

አቶ ተወገር ደመላ
የቦርድ አባል

አቶ ግዛቸው ቢተው
የቦርድ አባል

አቶ ታደሰ ከፋት
የቦርድ አባል

የስራ አመራር አባላት

አቶ የኋላ ገሠሠ
ዋና ስራ አስፈፃሚ

አቶ አብርሃም አጅጉ
የኮርፖሬት ባንኪንግ ዋና መኮንን

አቶ በለጠ ዳኘው
የሪቴይል ባንኪንግ ዋና መኮንን

አቶ በለጠ ቀኔ
የኮርፖሬት አገልግሎት ዋና መኮንን

አቶ ወንድይፍራው ታደሠ
የስትራቴጂ እና ማርኬቲንግ ዋና መኮንን

አቶ ኤልያስ ብርሃኑ
ዳይሬክተር - ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

አቶ አዳኛ አበበ
ዳይሬክተር - ቅርንጫፍ ማስተባበሪያ
እና ሃብት ማሰባሰብ

አቶ ተገኔ ሲሳይ
ዳይሬክተር- የሰው ኃይል
አስተዳደር

ወ/ሮ ጽጌ አያሌው
ዳይሬክተር - ዓለም አቀፍ የባንክ
አገልግሎት

የስራ አመራር አባላት

አቶ ክርስቲያን ካሳ
ዳይሬክተር- ማርኬቲንግ
እና ሪሰርች

አቶ ዳንኤል ለገሰ
ዳይሬክተር- ስትራቴጂ እና ኢኖቬሽን

አቶ ዳዊት አየነው
ዳይሬክተር- የውስጥ ኦዲት

አቶ ደሳለኝ አያሌው
ዳይሬክተር- ፋይናንስ

አቶ አቡበከር ናዚር
ዳይሬክተር- ከወለድ ነፃ
የባንክ አገልግሎት

አቶ አንዳክመው ጌትነት
ዳይሬክተር- ሀግ አገልግሎት

አቶ እዮብ ንጉሴ
ዳይሬክተር- ግዥ እና
ንብረት አስተዳደር

አቶ ፀጋ መኮንን
ዳይሬክተር- ሪስክ እና
ኮምፕሊያንስ

አቶ ሰለሞን ተፈራ
ዳይሬክተር- የብድር ትንተና፣ ወርክአውት
እና ፖርትፎሊዮ አስተዳደር

የስራ አመራር አባላት

አቶ አበባው አበበ
ዳይሬክተር - የደንበኞች ግንኙነት አስተዳደር

አቶ አርስቱ ወ/ማርያም
ዳይሬክተር - ዲጂታል ባንኪንግ

አቶ ሲሳይ ፀጋዬ
ሥራ አስኪያጅ - ባሕር ዳር ዲስትሪክት

አቶ ሳሙኤል ተሾመ
ሥራ አስኪያጅ - ደሴ ዲስትሪክት

አቶ ማርቆስ ደመቀ
ሥራ አስኪያጅ - ደቡብ ምዕራብ ዲስትሪክት

አቶ ስምኦን አበበ
ሥራ አስኪያጅ - ሰሜን ምስራቅ ዲስትሪክት

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር መልዕክት

የተከበራችሁ የባንካችን ባለአክሲዮኖች፣

የዓባይ ባንክን የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት ሳቀርብላችሁ ታላቅ ደስታና ኩራት ይሰማኛል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት የኮሮና ቫይረስን ሶስት ተከታታይ የወረርሽኝ ማዕበል ከማስተናገዱ ጋር ተያይዞ ዓለምአቀፍ ኢኮኖሚው ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖው የበረታበት ከመሆኑም ባሻገር በዓለምአቀፍ ደረጃ የተለየ አኗኗር እንዲለመድም ያስገደደ ሆኖ አልፏል፡፡ ወረርሽኙ የምንወዳቸውን በሞት በመንጠቅ፣ የስራ እንቅስቃሴን በመግታትና ማህበረሰብን እንዲሁም ቤተሰቦችን በመነጣጠልና ከግንኙነት በማቀብ ያደረሰውን ከባድ ጉዳት ተጋፍጠን ምንም እንኳን የስርጭት ሁኔታው ከሀገር ሀገር የተለያየ ቢሆንም ከክትባቱ መገኘትና መዳረስ ጋር ተያይዞ ዓለም በስተመጨረሻ ወረርሽኙ ካጠላባት ጨለማ እየወጣች እንደሆነ ይታያል፡፡ በወቅቱ ይፋ የተደረገው የዓለምአቀፉ የገንዘብ ተቋም (IMF) ሪፖርት ይህንን ከባድ ዓመት "አምሳያ የሌለው" ሲል የሰየመበት ሁኔታ በዓመቱ በወረርሽኙ ምክንያት የተስተናገደውን ከፍተኛ የቀውስ ደረጃ የሚናገር ነው፡፡

በሀገራችንም የታየው ችግር ከሞላ ጎደል በተመሳሳይነት ሊቀመጥ የሚችል ነው፡፡ ሀገራችን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሕግ ማስከበርና የህልውና ጦርነት ውስጥ ተጎትታ መግባቷ ከኮቪድ-19 አሉታዊ ተጽዕኖዎች ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መዳከምና የስራ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ አስከትሏል፡፡ ከእነዚህ ችግሮች ጋር በተያያዘ ለታየው አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ መዳከም ኢኮኖሚው በተለይም ሆቴልና ቱሪዝም እንዲሁም የትራንስፖርት ዘርፎች በተለየ ሁኔታ መጎዳታቸው ይታወቃል፡፡

በበጀት ዓመቱ መገባደጃ ላይ ከወለድ-ነጻ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ አንድ ተጨማሪ ባንክ ኢንዱስትሪውን የተቀላቀለ ሲሆን ይህም አጋጣሚ ከ20 በላይ የሚሆኑ ሌሎች በምስረታ ላይ የሚገኙና ከፊሎቹም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን (ኢብባ) የስራ ፈቃድ በማግኘት ላይ ያሉ አዳዲስ ባንኮች የዘርፉን ተሳታፊዎች በዕጥፍ ለማሳደግ በመምጣት ላይ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ በኢብባ አዲስ ባንክ ለማቋቋም የሚጠየቀው ዝቅተኛው የካፒታል መጠንም በከፍተኛ ደረጃ ከፍ የተደረገው እንዲሁም መንግስት የሀገራችንን የመገበያያ ገንዘብ የመቀየር ስራም በስኬት ያጠናቀቀው በዚሁ የበጀት ዓመት ነበር፡፡ ይህ ሁኔታም ከባንክ ስርዓቱ ውጭ የነበረን ገንዘብ በባንኮች እንዲዘዋወር ከማድረጉም በላይ ብሔራዊ የፋይናንስ ደህንነትን ከመጠበቅ አኳያ መልካም አጋጣሚና አይነተኛ ሚና የነበረው ስራ ነበር፡፡

የባንካችን የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም 10ኛውን ዓመት የምስረታ በዓሉን ባማረ ውጤት የታጀበ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የባንካችን አጠቃላይ አፈጻጸም በሚታወቁት መመዘኛዎች ሁሉ ሲታይ እጅግ አመርቂ ነበር፡፡ የተቀማጭ ገንዘብ ከማሰባሰብ አንጻር ባንኩ የ49 በመቶ አጠቃላይ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን አጠቃላይ ቁጠባውም ብር 23.9 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የብድር መጠኑም አስደማሚ የሆነ የ72 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ የባንካችን የደንበኞች ቁጥርም በዓመቱ በ46 በመቶ አድጎ 1.2 ሚሊዮን ላይ ደርሷል፡ ፡ የአገልግሎት መስጫ ቅርንጫፎቻችንንም በመላ ሀገሪቱ የማስፋፋት ሰፊ እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን በዓመቱ 63 አዳዲስ ቅርንጫፎች ተከፍተው አጠቃላይ የቅርንጫፎቻችንን ቁጥር ብዛትም 286 አድርሶታል፡፡ ከነዚህ ዋና ዋና እና በርካታ ሌሎች የስራ እንቅስቃሴዎች ጋር ተያይዞ ባንካችን በበጀት ዓመቱ የ80 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብና ለመጀመሪያ ጊዜ የአንድ ቢሊዮን አርከንን በማለፍ ብር 1.15 ቢሊዮን ትርፍ አስመዝግቧል፡፡

በተጠቃለለው የበጀት ዓመት ለደንበኞቻችን የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የምናደርገውን ጥረት ትርጉም ባለው መልኩ እገዛ ያደረጉ በርካታ ጉልህ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከነዚህም መካከል አዲስ የመዋቅር ጥናት ማስጠናትና መተግበር፤ የዋናውን ኮር ባንኪንግ ሲስተም ማዘመንና ማሻሻል፣ አዲስ የደሞዝ ስኬል መተግበር፣ የባንኩን የወደፊት ዋና መስሪያ ቤት ሕንጻ ግንባታ ለመጀመር የሚያስችል ኮንትራት ከታዋቂ ሕንጻ ተቋራጭ ጋር ስምምነት መፈረሙ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ዓመቱን ሙሉ የተከናወኑ እነዚህ የባንኩ ዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴዎች በጠንካራ የስጋት አስተዳደር እንዲሁም የኮምፕሊያንስ መልካም ተሞክሮዎችና አሰራሮች የተጠናከሩ ነበሩ፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ባንካችን የማሕበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አንጻር በበርካታ ሀገር አቀፍ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ በማድረግ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡

ዓመቱን አጠቃለን መጨውን ጊዜ ስንመለከት ለሀገራችን ሰላም በጋራ ለመስራት በመንቀሳቀስና በኮቪድ-19 የተደቀነብንን አደጋ በመዋጋት እንዲሁም ሌሎች ተግዳሮቶችን ተቋቁመን የዕድገት አቅጣጫችንን በማስጠበቅ እና በማጠናከር ለተሻለ ውጤት እንተጋለን፡፡ ሁሉንም ባለድርሻ አካላትና የባንኩን ማኅበረሰብ ከጎናችን በመያዝ የውስጥ ተቋማዊ ቁመናችንን በማጠናከርና የአፈጻጸም አቅማችንን በማጎልበት የባንካችንን የዕድገት መሪ ዕቅድ በማስቀጠል የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ በቁርጠኝነት እንቀሳቀሳለን፡፡

በመጨረሻም የባንኩን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ባለአክሲዮኖች እንዲሁም የስራ አመራር እና አጠቃላይ ሠራተኞች ለሳያችሁት ትጋትና ለተመዘገበው አስደሳች ውጤት እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚም የባንክ ዘርፉን ወደተረጋጋና ምቹ የስራ ከባቢ ከመምራት አንጻር ለተወሰዱ አጠቃላይ እርምጃዎች የኢብባን ማመስገን እወዳለሁ፡፡ ለአጠቃላይ የንግዱ ማኅበረሰብ እንዲሁም ውድ ደንበኞቻችን አብራችሁን ስለሰራችሁና የተሻለ እንድናገለግላችሁ ስለረዳችሁን ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

ኢትዮጵያ ታደሰ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር

የዋና ስራ አስፈጻሚ መልዕክት

የተከበራችሁ የባንካችን ባለአክሲዮኖች፣

የባንካችንን የ2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት በዓመቱ ከተከሰቱ አበይት ኩነቶች ጋር ሳቀርብላችሁ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ባስከተለው አስከፊ የሆነ ዓለምአቀፍ የጤናና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የተነሳ ዓመቱን ሙሉ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኖ አልፏል፡፡ እንደ ዓለምአቀፉ የገንዘብ ተቋም (IMF) ሪፖርት ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ ኢኮኖሚዎች ዝቅተኛ ዕድገት በማስመዝገባቸው የዓለም ዓመታዊ ዕድገት በዓመቱ መጨረሻ ወደ -3.1 በመቶ ወርዶ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ዓመቱ ከዚህ ቀደም ከታዩ ከቀውስ የማንሰራራት ጊዜያት ሁሉ አንጻር ሲታይ ፈጣኑ የኢኮኖሚ ማገገም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የ2021 የዕድገት ምጣኔው 5.6 በመቶ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ምንም እንኳን የክትባቱ ሥርጭትና ተደራሽነት ወጥ ያልሆነ ቢሆንም ለኢኮኖሚ ማገገሙ በዋናነት የሚጠቀስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የኢኮኖሚ ማንሰራራቱ ባደጉ ሀገራት ተጠናክሮ ሲታይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ግን ዝቅተኛ ነበር፡፡

እንደ ዓለም ባንክ የ2021 ሪፖርት የኮቪድ-19 ስርጭት ከሳሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ቀደም ብሎ ከተጠበቀው በታች መሆን በአካባቢው ጠቅላላ ምርት (GDP) እድገት ላይ አምብዛም ተጽዕኖ ሳያሳድር ይልቁንም በአርሻና የሸቀጦች ዋጋ ላይ የተጠናከረ ዕድገት ታይቷል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም ወረርሽኙ ቀስ በቀስ በመስፋፋት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕይወት በመቅጠፍ ሀገራችንን በአፍሪካ በከፍተኛ ደረጃ ከተጠቁ አራቱ ሀገራት መካከል አስቀምጧታል (አፍሪካ ሲዲሲ)፡፡ በዓመቱ ማገባደጃ ላይ በአዲሱ የዴልታ ቫይረስ ዝርያ አማካኝነት የወረርሽኙ ሶስተኛ ማዕበል ተቀስቅሶ ተጨማሪ ሕይወት መቅጠፍ ጀምሯል፡፡ የንግድ እንቅስቃሴን በማዳከምና አጠቃላይ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ በማስከተል የበሽታው አሉታዊ ተጽዕኖዎች በኢኮኖሚያችን ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል፡፡ በተጨማሪም በሀገራችን የሰሜኑ ክፍል ከጥቅምት 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የሕግ የማስከበርና የሳልውና ጦርነት ከመከሰቱ ጋር ተያይዞ ኢኮኖሚው ተጨማሪ መሰናክል ገጥሞት ቆይቷል፡፡ ምንም እንኳን እንደ ሆቴልና ቱሪዝም እንዲሁም ትራንስፖርት ያሉ ትላልቅ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተዳከመ እንቅስቃሴ ቢታይባቸውም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የ6.1በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ አመታዊው የዋጋ ግሽበትም ዓመቱን ሙሉ በሁለት አኃዝ ደረጃ ሲታይ ቆይቷል፡፡

በተለያየ የምስረታ ደረጃ ላይ የሚገኙ ብዛት ያላቸው አዳዲስ ባንኮች ዘርፉን ለመቀላቀል መነሳታቸውን ተከትሎ የባንክ ኢንዱስትሪው በዕጥፍ ለማደግ ጫፍ ላይ ደርሷል፡፡ በዓመቱ በዘርፉ ለተመዘገበው አመርቂ የተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ አፈጻጸም የባንኮች ተወዳዳሪነት መጨመርና የመንግስት የፖሊሲ ማስተካከያዎችና እርምጃዎች በዋናነት ተጠቃሽ ነበሩ፡፡ በዚህም የተነሳ ዘርፉ በሁሉም ዋና ዋና መመዘኛዎች በሚባል ደረጃ ማለትም በተቀማጭ ገንዘብ፣ በብድር፣ ካፒታል፣ በቅርንጫፍ ማስፋፋት እንዲሁም በጠቅላላ የትርፍ መጠን ጥሩ የሚባል ዕድገት አስመዝግቧል፡፡

ባንካችንም ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪው ዕድገት የሚገባውን ድርሻ በመውሰድ የ10ኛ ዓመት በዓሉን አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ አድምቆታል፡፡ በአመቱ 63 አዳዲስ ቅርንጫፎች በመላ ሀገሪቱ መክፈታቸው፤ በሌሎች የኮርፖሬትና በቅርንጫፎች ደረጃ በተከናወኑ ዓበይት ተግባራት በመታገዝ ባንካችን የተቀማጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ረገድ ከፍ ያለ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ይህም የ49 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ አጠቃላይ የቁጠባ መጠኑን ብር 23.9 ቢሊዮን አድርሶታል፡፡ ባንኩ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ፋይናንስ በማድረግ የብድር መጠኑን በብር 8.4 ቢሊዮን አሳድጎ ጠቅላላ ብድሩንም ብር 20.1 ቢሊዮን በማድረስ የ72 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡ ፡ በትርፍ በኩልም የታየውም የ80 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ከታክስ በፊት የተገኘውን የትርፍ መጠን ብር 1.15 ቢሊዮን አድርሶታል፡፡

ባንካችን በስጋት አስተዳደርና ኮምፕሊያንስ አሰራር ዙሪያ በሠራተኞች ዘንድ አጠቃላይ ግንዛቤን በሚፈለገው ደረጃ ከመፍጠር እንዲሁም ሽብርተኝነትንና የሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ከመከላከል አንጻር ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ያለው ዘመናዊ መተግበሪያ ሥራ ላይ በማዋል ጠቃሚ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ የማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻርም ባንካችን በርካታ ሀገር አቀፍ እንቅስቃሴዎች ላይ በሰፊው የተሳተፈ ሲሆን በበጀት ዓመቱ እስከ ብር 33.5 ሚሊዮን የሚሆን ገንዘብ ለተለያዩ የበጎ-አድራጎት ተግባራት ይውል ዘንድ ለግሷል፡፡

ያሳለፍነው 2013 ዓ.ም የበጀት ዓመት በአጠቃላይ ሲታይ ፍሬያማ የነበረ ሲሆን በአዲሱ የስራ ዓመት መባቻ ግን ከፊታችን ፈታኝ ተግዳሮቶች ይጠብቁናል፡፡ አዲስ የጀመርነው የበጀት አመት በአዲሱ የዴልታ ቫይረስ ዝርያ ሳቢያ ዳግም የተቀሰቀሰው የኮሮና ወረርሽኝ ስርጭት ጥላ አጥልቶበታል፡፡ በኢኮኖሚውም ረገድ የሀገራችን ሰላምና ደህንነት እንደሚሻሻልና የስራ አድል እንደሚስፋፋ፣ የዋጋ ግሽበቱም እየቀነሰ በመሄድ ሀገራዊ ቁጠባንም እንደሚያበረታታ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ተግዳሮቶቻችንን በብልሃት በማለፍና ከነባራዊው ከባቢ የምናገኛቸውን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም በደንበኞቻችን፣ በባለአክሲዮኖች እንዲሁም አጠቃላይ ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት ድጋፍና እገዛ ለተሻለ ውጤት እንተጋለን፡፡

ለመላ የባንካችን ሠራተኞች፣ የሥራ አመራር እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓባላት ለባንካችን ውጤታማነት ላበረከታችሁት አስተዋጽኦ ልባዊ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ ያለጥርጥር፣ ደንበኞቻችን የስኬታችን ዋነኞቹ ምንጮች ናቸውና በቀጣይ ጊዜያት የለቀና የዘመነ የባንክ አገልግሎት በማቅረብ ውለታቸውን እንከፍላለን፡፡ በዚህ አጋጣሚም የባንካችንን ባለአክሲዮኖች እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ሥራችንን በስኬት እንድንወጣ ስለረዳችሁን ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

የኋላ ገሠሠ
ዋና ሥራ አስፈጻሚ

የዓበይት ክንውኖች አጭር መግለጫ



ተቀማጭ ገንዘብ (በሚሊዮን ብር)



ጠቅላላ ብድርና የብሔራዊ ባንክ ቢል (በሚሊዮን ብር)



ጠቅላላ ገቢ (በሚሊዮን ብር)



ትርፍ ከግብር በፊት (በሚሊዮን ብር)



ጠቅላላ ሃብት (በሚሊዮን ብር)



የተከፈለ ካፒታል (በሚሊዮን ብር)



ጠቅላላ ሰራተኞች ብዛት



የደንበኞች ብዛት



የቅርንጫፍ ብዛት



የባለአክሲዮኖች ብዛት

የቦርድ አባላት ስብሰባ

የስራ አመራር አባላት

የሸሪዓ አማካሪ ቦርድ

የአሬተኛ ዙር ይመንዝሩ ይቀበሉ የሽልማት ስነ-ስርዓት

ዓባይ ባንክ
Abay Bank

ጊዜ እና ቦታ ሳይገድብዎ ሂሳብዎን ያንቀሳቅሱ
ACCESS YOUR ACCOUNT WHEREVER,WHENEVER



ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ
Abay - The Trustworthy Bank
Tel +251 11 515 8961, +251 11 554 9735 E-mail: info@abaybank.com.et
Ziquala Complex, Jomo Kenyatta Avenue, ADDIS ABABA, ETHIOPIA
web: www.abaybank.com.et

/abaybanksharecompany
/AbayBank
@AbayBank
/abaybanksharecompany
/In/abaybank

ዓባይ ባንክ
Abay Bank

ክፍል 1

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

ክፍል1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2021 ዓ.ም የተጠናቀቀውን የባንኩን ዓመታዊ የስራ ክንውን እና የኦዲተሮች ዝርዝር ሪፖርት እንደሚከተለው ሲያቀርብ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል፡፡ በሪፖርቱ የመጀመሪያ ክፍል የባንኩ ዓመታዊ አፈጻጸም በአጭሩ የሚቀርብ ሲሆን በክፍል ሁለት ላይ ጠቅለል ያለ የኦዲተሮች ሪፖርት ተካትቶ ቀርቧል፡፡

1.1. ኦፕሬሽናል ክንውኖች

1.1.1. የተቀማጭ ገንዘብ ክንውን

በተጠናቀቀው ዓመት ባንኩ ካስመዘገባቸው አመርቂ ውጤቶች መካከል የተቀማጭ ሂሳብ አፈጻጸም አንዱ ሲሆን በዓመቱ ውስጥ ተጨማሪ 7.8 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የባንኩ አጠቃላይ የመደበኛ እና ከአባይ ሳዲቅ ከወለድ ነጻ ተቀማጭ ሂሳብ ጋር ተዳምሮ ብር 23.9 ቢሊዮን ደርሷል፡፡

ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ49 በመቶ ዕድገት የተመዘገበበት ነው፡፡ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ በመደበኛው የቁጠባ ሂሳብ የተሰበሰበው ተቀማጭ ከቀዳሚው ዓመት የ48 በመቶ ዕድገት በማሳየት ብር 22.6 ቢሊዮን ማደረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይም ከወለድ ነጻ አገልግሎት ደንበኞች የቆጠቡት ገንዘብ መጠን ብር 1.3 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ዓመታዊ ዕድገቱም 71 በመቶ ደርሷል፡፡ በዓመቱ ውስጥ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ተቀማጭ መካከል የቁጠባ ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ብር 18 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከቀዳሚው ዓመት የ50 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል የተንቀሳቃሽ ሂሳብ የ68 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ አጠቃላይ ተቀማጭ ብር 5 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በአንጻሩ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ካለፈው ዓመት የ16 በመቶ ቅናሽ በማስመዝገብ አጠቃላይ መጠኑ ወደ ብር 891 ሚሊዮን ዝቅ ብሏል፡፡

በተጠናቀቀው ዓመት ከ376,000 በላይ አዳዲስ ደንበኞችን በማፍራት የባንኩን የመደበኛና የአባይ ሳዲቅ ከወለድ ነጻ አስቀማጭ ደንበኞች ቁጥር 1,201,319 ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም በዓመቱ የ46 በመቶ ጭማሪ የተመዘገበበት ሲሆን የደንበኞቻችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ማደግ ለተቀማጭ ገንዘቡ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ አንደኛው ምክንያት ነው፡፡

ምስል 1. የተቀማጭ ገንዘብ ንጽጽር በዓይነት



ባለፉት ዓመታት የባንኩ የተቀማጭ ሒሳቦች ድርሻ መጠነኛ ለውጥ በማስመዝገብ ዋነኞቹ የቁጠባ እና የተንቀሳቃሽ የተቀማጭ ሂሳቦች ድርሻ እንደየቅደም ተከተላቸው የ76 በመቶ እና የ21 በመቶ ድርሻ በመውሰድ የባንኩ ተቀማጭም ሆነ ተያያዥ ወጭ በአንጻራዊነት የተረጋጋ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል ባንኩ በተከተለው አቅጣጫ በዓመቱ ውስጥ የጊዜ ገደብ ተቀማጭን ድርሻ ወደ 3 በመቶ ዝቅ ማድረግ ችሏል፡፡



ምስል 2. የተቀማጭ ገንዘብ በዓይነት ድርሻ

1.1.2. የብድር አገልግሎት

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ባንኩ ለመደበኛውም ሆነ ለአባይ ሳዲቅ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ያቀረበው የብድር መጠን ዓመታዊ የ72 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 20.1 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከአጠቃላይ የብድር መጠን ውስጥ ለመደበኛ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎች ያቀረበው የብድር መጠን ብር 19.6 ቢሊዮን በመያዝ ከፍተኛው ሲሆን ቀሪውን ብር 538 ሚሊዮን ለወለድ ነጻ ተገልጋዮች ተደራሽ የሆነ ነው፡፡

ባንኩ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ለቀረቡ አዋጭ የብድር ጥያቄዎች ድጋፍ በመስጠት በዘርፎች መካከል ያለውን የብድር ስርጭት ሚዛናዊ ለማድረግ ያስቀመጠውን አቅጣጫ ለማሳካት ያደረገው ጥረት ለየዘርፎቹ ያቀረበው የብድር መጠን አመታዊ ዕድገት እንዲያስመዘግብ አስችሎታል፡ ፡ አባይ ባንክ ካቀረበው የብድር መጠን ውስጥ የዓለም ዓቀፍ ንግድ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ደንበኞች ያቀረበው የብድር መጠን ከአጠቃላዩ የ42 በመቶ ድርሻ በመያዝ ቀዳሚ ሲሆን ይህም ለዘርፉ የተሰጠውን ሀገራዊ አቅጣጫ የተከተለ ነው፡፡ ባንኩ ለሃገር ውስጥ ንግድና አገልግሎት ያቀረበው የብድር መጠን በ20 በመቶ ድርሻ የሚከተል ሲሆን ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የቀረበው ብድር የ16 በመቶ ይይዛል፡፡ የማምረቻ እና ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እያንዳንዳቸው የ8 በመቶ ድርሻ ሲወስዱ ለትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ የቀረበው ብድር መጠን ቀሪውን የ6 በመቶ ድርሻ ወስዷል፡፡

ባንኩ የተከተለው ጤናማ የሆነ የብድር አስተዳደር ስርዓት የብድሩን ጤናማነት በከፍተኛ ደረጃ ማረጋገጥ ያስቻለው ሲሆን ይህም ተቆጣጣሪው አካል ጤናማ ላልሆኑ ብድሮች ካስቀመጠው ምጣኔ ዝቅተኛ መለኪያ አንጻር ጤናማ ብድር ማስተዳደር መቻሉ ዋነኛው ማመላከቻ ነው፡፡

ምስል 3፡- የብድር ስብጥር በኢኮኖሚ ዘርፎች (በሚሊዮን ብር)



በባንኩ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች

1.1.3. የዓለም አቀፍ ባንክ አገልግሎት

ምንም እንኳን ኮቪድ-19 በዓለምአቀፍ ንግድ ላይም ሆነ በገንዘብ ዝውውሩ ላይ ያስከተለው ከፍተኛ ተጽእኖ ባንካችን ካጋጠመው አስተማማኝ የኮረስፖንደንት ባንኮች እጥረት ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ ተግዳሮት የፈጠረብን ቢሆንም ባንካችን በዓመቱ ውስጥ ማፍራት የቻለው የውጭ ምንዛሪ ከቀዳሚው ዓመት የ27 በመቶ ዕድገት የተመዘገበበት ነው፡፡

ባንካችን የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ለማሳደግ የሚረዱ በርካታ ጥረቶች ያከናወነ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለአራተኛ ተከታታይ ዓመት የውጭ ምንዛሪ ለሚያስገኙ ደንበኞች ያቀረበው የሽልማት ማበረታቻ፤ ከተጨማሪ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች እና በዓለምአቀፍ ደረጃ ከሚሰሩ ኮረስፖንደንት ባንኮች ጋር በጥምረት ለመስራት ያደረጋቸው ጥረቶች ሁነኛ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

1.2. የገንዘብ-ነክ ክንውኖች

1.2.1. ገቢ

ባንኩ በዓመቱ ውስጥ የብር 3.4 ቢሊዮን ገቢ በመሰብሰብ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ የ63 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ገቢ ውስጥ ከወለድ የተገኘ ገቢ የ 72 መቶኛ ድርሻ በመውሰድ ከቀዳሚው ዓመት ጋር ተመሳሳይ ድርሻ አስመዝግቧል፡፡ በሌላ በኩል ከኮሚሽን እና አገልግሎት እንዲሁም ከሌሎች የገቢ ምንጮች የተገኘው ገቢ ከቀዳሚው ዓመት መጠነኛ የድርሻ ሽግሽግ በማድረግ በዓመቱ የ19 በመቶ እና የ9 በመቶ ድርሻ ወስደዋል፡፡



ምስል 4. የገቢ ስብጥር

1.2.2. ወጪ

ካለፈው ዓመት የ56 በመቶ ጭማሪ ያስመዘገበው የባንኩ ዓመታዊ ወጪ ብር 2.3 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ዓመታዊ የወጪ ዕድገት ከቀዳሚው ዓመት ጋር ሲገናዘብ ባንኩ ለብድር መጠባበቂያ ያዋለው ወጪ የ49 በመቶ ጭማሪ በማሳየት ከፍተኛ ዕድገት ያሳየ ሲሆን የባንኩ ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች በ82 በመቶ ጭማሪ ተከታዩን ደረጃ ወስዷል፡፡ በተጨማሪም ባንኩ ለደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ ያዋለው ወጪ የ54 በመቶ ዕድገት የታየበት ሲሆን ለወለድ ክፍያ የወጣው ወጪ ደግሞ የ42 መቶኛ ዕድገት ተመዝግቦበታል፡፡

በሌላ በኩል ዋነኞቹ የወጪ ምክንያቶች ከአጠቃላይ ወጪ አንጻር የወሰዱት ድርሻ ሲመዘን የ36 በመቶ ድርሻ በመውሰድ የወለድ ክፍያ ቀዳሚ ሲሆን ለደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ወጪ በ31 በመቶ ድርሻ ይከተላል፡፡ አስተዳደራዊ ወጪዎች በ28 በመቶ ድርሻ እና የብድር መጠባበቂያና ሌሎች ወጪዎች በ5 በመቶ ድርሻ በአንጻራዊነት በአመቱ ውስጥ ዝቅ ያለ የወጪ አስተዋጽኦ አስመዝግበዋል፡፡

ምስል 5፡- ወጪዎች (በሚሊዮን ብር)



1.2.5 ትርፍ

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ባንኩ በታሪኩ ከፍተኛውን የትርፍ መጠን በማስመዘገብ ከግብር በፊት የተገኘውን ትርፍ ብር 1.15 ቢሊዮን አድርሷል፡፡ ይህም ከቀዳሚው ዓመት የ80 በመቶ ወይንም የ513 ሚሊዮን ጭማሪ የተመዘገበበት ነው፡፡

ምስል 6. ከግብር በፊት ትርፍ (በሚሊዮን ብር)



1.2.3. ጠቅላላ ሃብት

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2021 ዓ.ም. የተመዘገበው የባንኩ አጠቃላይ ሃብት ብር 29.9 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ የባንኩ አጠቃላይ ሃብት የ48 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ወይንም የብር 9.8 ቢሊዮን ጭማሪ የተመዘገበበት ሲሆን በዓመቱ ውስጥ ባንኩ ያቀረበው የብድር መጠን ዕድገት ለአጠቃላይ ሃብት ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

1.2.4. ካፒታል

የባንኩ አጠቃላይ ካፒታል የ37 በመቶ ጭማሪ በማሳየት ብር 4.2 ቢሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡ በተያያዥም የባንኩ ባለአክሲዮኖች የብር 642 ሚሊዮን ተጨማሪ ድርሻዎችን በመግዛት የባንኩን የተከፈለ ካፒታል ማሳደግ የቻሉ ሲሆን ዓመታዊ የ30 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ብር 2.8 ቢሊዮን ደርሷል፡፡

1.3 ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ክንውኖች

1.3.1 ቅርንጫፍ ማስፋፋት

የቅርንጫፍ ቁጥሩን ይበልጥ በማሳደግ ባንኩ ወደ ደንበኞቹ ይበልጥ ለመቅረብ የሚያደርገውን ጥረት በተጠናቀቀው የበጀት ዓመትም የቀጠለበት ሲሆን በዓመቱ ውስጥ ከመደበኛ ቅርንጫፎች በተጨማሪ ከወለድ ነጻ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ቅርንጫፎችን ጨምሮ በአጠቃላይ 63 ተጨማሪ ቅርንጫፎችን አዋጭ በሆኑ አከባቢዎች ላይ በመክፈት አገልግሎት አስጀምሯል። በአጠቃላይ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ቅርንጫፎች ቁጥርም የ28 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ 286 ማድረስ ተችሏል። ከነዚሁ ቅርንጫፎች መካከልም ስድስቱ ቅርንጫፎች በተለይ የዓባይ ሳዲቅ አገልግሎት ብቻ የሚሰጥባቸው ቅርንጫፎች ሲሆን በ251 ቅርንጫፎቻችን ከወለድ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ መስኮቶችን በተጨማሪ በመክፈት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

የቅርንጫፍ አከፋፈት ስነ ስርዓት

1.3.2 የሰው ኃይል

በተጠናቀቀው ዓመት ባንኩ ለተጨማሪ 1,379 ዜጎች አዲስ የስራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን አጠቃላይ የባንኩ ሰራተኞች ብዛት 5,307 ደርሷል። ከባንኩ የሰው ኃይል መካከል 2,757 ሰራተኞች በቋሚነት የሚያገልገሉ ሲሆኑ 2,550 ሰራተኞች በቀጣሪ ድርጅቶች የሚተዳደሩ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ናቸው። ባንኩ በዓመቱ የፈጠረው ተጨማሪ የስራ ዕድል ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ35 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል።

የአንድ ተቋም ስትራቴጂያዊ ፍላጎት ለማሳካት ከሚረዱ ወሳኝ ቁልፍ ጉዳዮች መካከል ተወዳዳሪ የሆነ፣ ትጉህ እና የተነቃቃ የሰው ሃብት መፍጠር ዋነኛው ነው። ይህን ከግምት በማስገባትም ባንኩ ብቃት ያለው ሰራተኛ መሳብ የሚያስችል እንዲሁም የሰው ሃይል ልማትን ታሳቢ ያደረገ ተከታታይ የስልጠና ስርዓት በመዘርጋት ከአጠቃላይ የሰው ሃይሉ 96 በመቶው ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሰራተኛ ማካበት የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም በዓመቱ ውስጥ ለ2,156 ሰራተኞቹ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት ችሏል። ብቃት ያላቸውን ሰራተኞች በባንኩ እንዲቆዩ ከማስቻል አንጻር እና ውጤታማነት ከማሳደግ አንጻር ባንኩ በዓመቱ ውስጥ አጠቃላይ የመዋቅር ክለሳ ያደረገ ሲሆን ለሰራተኞቹም የደመወዝ ማሻሻያ አድርጓል።

1.3.3 የዲጂታል-ባንኪንግ አገልግሎት

ባንኩ የዲጂታል አቅሙን ለማዘመንና ለማጎልበት ያስችለው ዘንድ ለዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ግዢ፣ ለሴክተሩ የደህንነት ክፍተት ማጠናከሪያ እና ለአቅም ግንባታ የሚውል ከፍተኛ ገንዘብ ፈሰሰ አድርጓል። ይህን ተከትሎም ባንኩ በዓለማችን ታዋቂ ከሆነው ኦራክል ሲስተምስ ግዢ በመፈጸም የኮር-ባንኪንግ ስርዓቱን ማዘመን የቻለ ሲሆን የትግበራ ፕሮጀክቱንም በሚያስመስግን መልክ በመተግበር ውጤታማ ሽግግር በማድረግ የኮር-ባንኪንግ ስርዓቱን ውጤታማ ከማድረግ በዘለለ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ከዚሁ የኮር-ባንኪንግ መስጠት አስችሎታል። ለውጤታማ የፕሮጀክት ትግበራ ባንካችን ከኦራክል የመልካም አፈጻጸም ዕውቅና ተሰጥቶታል።

በሌላ በኩል የባንኩን የመረጃ ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር ባንኩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠትና ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ የባንኩን የመረጃ ደህንነት ለማጠናከር የሚረዱ የኤቲኤም እና ዋፍ ማሽኖችን በማከናወን መተግበር የተቻለ ሲሆን በውስጥ አቅም የአደጋ ተጋላጭነት ምልከታ ተሰርቷል። በተጨማሪም በውስጥ አቅም የባንኩን ሲስተሞች ከተቆጣጣሪው አካልም ሆነ ከሌሎች ተቋማት ጋር የማስተሳሰር ስራ፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ አዳዲስ ሲስተሞችን የማበልጸግና ሌሎች ሲስተሞችን የማሳደግ ስራዎችን በዓመቱ ውስጥ ማከናወን ችለናል።

የዲጂታል ተደራሽነትን ከማስፋፋት አንጻር በተለያዩ አከባቢዎች ተጨማሪ የኤቲኤም ማሽኖችን በመትከል ለአገልግሎት ያበቃ ሲሆን በአባይ በደጀ አገልግሎት በኩል በሁሉም የሃገሪቱ አከባቢዎች የኤጀንት ባንኪንግ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት ተደርጓል።

በተያያዘም በዓመቱ ውስጥ እነኝህን የዲጂታል አገልግሎት የሚጠቀሙ ደንበኞቻችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል። በዚህም መሰረት የሞባይል ባንኪንግ ደንበኞች ቁጥር ካለፈው ዓመት የ85 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ 303,021 የደረሰ ሲሆን የካርድ ባንኪንግ ተገልጋዮች ቁጥርም የ 63 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማሳየት 273,569 ደርሷል። በተመሳሳይም የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚዎች ቁጥር 5,146 የደረሰ ሲሆን የደንበኞቻችን የአገልግሎት አጠቃቀም ልምድ በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል።

1.3.4 ማህበራዊ ኃላፊነት

ባንኩ ከዋነኞቹ እሴቶቹ መካከል አንዱ የሆነውን ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን በፍትሃዊነት በማዳረስ እና አገልግሎቱን ማህበረሰባዊ ኃላፊነትን በሚያረጋግጥ መንገድ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ማህበረሰባዊ ደህንነትን ከማስጠበቅ አንጻር ባንኩ ለሚያገለግለው ማህበረሰብ መልሶ የመስጠት ባህልን ያዳበረ ሲሆን ባንኩ የአስረኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ምክንያት በማድረግም ድጋፍ ለሚሹ ልዩ ልዩ የማህበረሰባችን አካላት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የብር 33.5 ሚሊዮን ድጋፍ አበርክቷል፡፡

የባህርዳር ታላቁ ሩጫ ተሳትፎ

1.3.5 ሪስክ ማኔጅመንት እና ኮምፕሊያንስ

ባንኩ በቀን ተቀን የስራ ሂደቱ ለሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሁሌም የራሱንም ሆነ የተቆጣጣሪው አካል መመሪያዎችን አክብሮ መስራትን ከሁሉም የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ለዚህም ይረዳው ዘንድ የተለያዩ መመሪያዎችን፣ ፖሊሲዎችን እና አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ጠንካራ የሪስክ አስተዳደር ስርዓት መገንባቱን ቀጥሎበታል፡፡

በዓመቱ ውስጥም በርካታ የሪስክ ደረጃ ግምገማ በማከናወን፣ የውስጥ መመሪያዎችን በመከለስ፣ የሪስክ ግምገማ መሰረቱን በማስፋት፣ አዳዲስ አሰራር ስርዓትን በማስተዋወቅ እና በሀሉም የስራ ሃላፊነቶች ለሚገኙ የባንኩ ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት የሪስክ አስተዳደር ስርዓቱን የበለጠ በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሪስክ አስተዳደር ስርዓቱን የሚያግዝ ሶፍትዌር ወደ ስራ አስገብቷል፡፡

1.3.6 የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች

የባንኩን የሃብት መሰረት ለማስፋት እና ምቹ የስራና የአገልግሎት ከባቢ መፍጠር እንዲያስችለው በማሰብ ባለፉት አመታት የግንባታ ቦታዎችን የማስከበር እና የቅድመ ግንባታ ስራዎችን የማጠናቀቅ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ ይህን ተከትሎም የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት እና የደሴ ጽህፈት ቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች የቅድመ ግንባታ ስራዎች ሂደት ተጠናቅቆ በያዝነው የበጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የግንባታ ስራዎች የሚጀመሩ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የባንኩ የባህር ዳር ሁለገብ አገልግሎት ህንጻ እና ባንኩ በጎንደር ከተማ የገዛውን ህንጻ ቀሪ ስራዎች ማጠናቀቅ በተያዘው ዓመት የሚከናወን ይሆናል፡፡

1.4 ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

የሚቀጥሉት ወራት የባንኩ ዘርፍ የውድድር መድረክ የበለጠ እየከረረ እንደሚሄድ አመላካች ከሆኑት መካከል አንደኛው በርካታ ቁጥር ያላቸው አዳዲስ ባንኮች መስኩን መቀላቀላቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ በሌላም በኩል የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በማህበራዊና እና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ሊያስከትል የሚችላቸው ተፅዕኖዎችና በሃገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ያሉት አለመረጋጋቶች ስጋት የሚደቅኑ ናቸው፡፡

በአንጻሩም የሃገራችን መንግስት አለመረጋጋቶችን ለመቆጣጠር እያደረገው ያለው ጥረትና ኢኮኖሚያዊ መዛባቶችን ለማስተካከል እየተገበረ የሚገኘው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ውጤት እንደሚያስመዘግብ ይታመናል፡፡

ቀጣይ ዓመት ባንኩ በኢንዱስትሪው ውስጥ ካሉት ተወዳዳሪዎች በመጀመሪያው ረድፍ ከሚሰለፉት መካከል እንዲሆን ሌላ ዕድል ይሰጠዋል፡ ፡ ባንኩም ባለፉት ዓመታት በአብዛኞቹ መለኪያዎች ያስመዘገባቸውን መልካም ውጤቶች በማስቀጠል በስትራቴጂክ ዕቅዶቹ የነደፋቸውን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት የሚያደርግ ይሆናል፡፡ በተያያዝነው ዓመት በሃገራዊው ምርጫ አሸናፊ የሆነው ፓርቲ አዲስ መንግስት በመመስረት ሃገሪቱ የተረጋጋች እንድትሆን እና የሃገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲነቃቃ ምክንያት ይሆናል ብለን እንጠብቃለን፡፡

ይሁንና ቀጣዩ ዓመት ከተግዳሮቶች የጸዳ ሊሆን እንደማይችል እንገነዘባለን፡፡ በሚቀጥለው ዓመት አዳዲስ ባንኮች የተለየ አገልግሎት በማቅረብም ሆነ የተመረጡ ገበያዎችን ለይቶ ከማገልገል አንጻር በዘርፉ ጠንካራ ፉክክር እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን የኮቪድ 19 እና በሃገራችን ሰሜናዊ ክፍል እየተካሄደ የሚገኘው ጦርነት ኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ ሌላኛው ተግዳሮት ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

ዓባይ ባንክ
Abay Bank

ክፍል 2

የኦዲተሮች ሪፖርት

የዓባይ ባንክ የወደፊት ዋና መስሪያ ቤት ህንፃ ዲዛይን - አዲስ አበባ

የዓባይ ባንክ የወደፊት ህንፃ ዲዛይን - ባህርዳር

የዓባይ ባንክ የወደፊት ህንፃ ዲዛይን-ደሴ

TMS Plus
Tafesse,Shisema and Ayalew Certified Audit Partnership
Chartered Certified Accountants (UK) and Authorised Auditors (Ethiopia)
Member Firm of HLB International
THE GLOBAL ADVISORY AND ACCOUNTING NETWORK
HLB Ethiopia
Tel. 251-011-8961752 /011 6180638 Mob. 0911 229425 /0930 034356/0930 034357 Fax: 251-011 662 12 70/60
E-mail:- tmsplus@ethionet.et / tafessef@hotmail.com P.O.Box 110690 Addis Ababa - Ethiopia

የዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ለ2013 የበጀት አመት በተዘጋጀው ሂሳብ ላይ የቀረበ የውጭ
<u>ኦዲተሮች ሪፖርት በሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት ላይ የቀረበ ሪፖርት</u>

የሙያ አስተያየት

ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡትንና እ.አ.አ ጁን 30/ 2021 (በእኛ አቆጣጠር ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም) ለተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የተዘጋጁትን የዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር የሀብትና ዕዳ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሳራ እና ሌሎች ጠቅላላ ገቢዎች መግለጫ፤ በተጣራ ሃብት ላይ የታየ ለውጥ መግለጫ ፤ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ እንዲሁም ኩባንያው የሚከተላቸውን የሂሳብ አሰራር ፖሊሲዎች እና ማብራሪያዎች ያካተቱትን የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት አድርገናል፡፡

በእኛ አስተያየት ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎችና አባሪዎቻቸው አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን (IFRS) ተከትለው የተዘጋጁ ሲሆኑ በአጠቃላይ አክሲዮን ማህበሩ እ.አ.አ ጁን 30/ 2021 የነበረውን ሀብትና ዕዳ እንዲሁም በዚያው ዕለት ላለቀው ዓመት የነበረውን የሂሳብ እንቅስቃሴ እና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት በሚገባ ያሳያሉ፡፡

የአስተያየታችን መሰረት

የኦዲት ስራችንን ያከናወንነው አለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል ሲሆን በእነዚህ ደረጃዎች መሰረት የሚጠበቅብን ኃላፊነት ከዚህ በታች የኦዲተሮች ሃላፊነት በሚለው ርዕስ ስር ተመልክቷል፡፡ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች የስነምግባር ደረጃዎች ቦርድ ለሂሳብ ባለሙያዎች ያወጣው የስነ-ምግባር ኮድ በሚጠይቀው እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለተካሄደው ኦዲት አስፈላጊ በሆኑት የስነምግባር መርሆዎች መሰረት ከአክሲዮን ማህበሩ ነጻ እና ገለልተኛ ሆነን ስራችንን አከናውነናል፡፡ እንዲሁም የስነምግባር ደንቡ የሚጠይቃቸውን እና የሚጠበቁብንን ሌሎች ኃላፊነቶች አሟልተናል፡፡

ከዚህ በላይ የሰጠነው የሙያ አስተያየት ደረጃውን ተከትለን ባከናወንነው የኦዲት ስራና በቀረበልን የኦዲት ማስረጃ በመተማመን ነው፡፡

ቁልፍ የኦዲት ጉዳዮች

ቁልፍ የኦዲት ጉዳዮች የሚባሉት በእኛ ሙያዊ ግምት በአመቱ የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት ወቅት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት እና በዚሁ መነሻነት የሙያ አስተያየት ለመስጠት አጠቃላይ ትኩረት የተሰጣቸው ቢሆኑም በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተናጠል አስተያየት አልሰጠንም ፡፡

በሂሳብ ማብራሪያዎች ተራ ቁጥር 11 እና 12 እንደተገለፀው የብድር መጠባበቂያ ወጪ /ኢምፔይርመንት ሎስ/አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9 (IFRS 9) (ፋይናንሻል ኢንስትሩመንት) መሰረት አድርጎ የተወሰነ ነው፡፡ ይህ ቁልፍ የኦዲት ጉዳይ ተደርጎ የተወሰደበት ምክንያት አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9 (IFRS 9)(ፋይናንሻል ኢንስትሩመንት) የመጠባበቂያ ወጪን ለመወሰን መሰረታዊ የግምት ስራ የሚጠይቀው ውስብስብ ደረጃ በመሆኑ ነው ፡፡

በተጨማሪም በሒሳብ መግለጫ ተራ ቁጥር 37 ላይ እንደተገለጸው ለኮንስትራክሽን ኩባንያዎች የተሰጠው የሥራ አፈጻጸምና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደ ውሉ እንዲፈፀም ባንኩ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥብቅ ክትትልና እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

የኦዲት አሰራር ስርዓት

የብድር መጠባበቂያ ወጪ /ኢምፔይርመንት ሎስ/በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9 (IFRS 9) (ፋይናንሻል ኢንስትሩመንት) መሰረት አድርጎ የተሰላ መሆኑን ለማረጋገጥ የታሳቢዎቹን አግባብነት ለመገምገም የሚያስችል የኦዲት አሰራር ስርዓት ተከትለናል ፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን በተመለከተ የዳሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት

አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን በመከተል የሂሳብ መግለጫዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ እንዲሁም ሆን ተብሎም ሆነ ወይንም በስህተት ከሚፈፀም ጉልህ ስህተት ነፃ የሆኑ የሂሳብ መግለጫዎችን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶች መዘርጋት የባንኩ የዳሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት ነው፡፡ ቦርዱ የሂሳብ መግለጫዎችን በሚያዘጋጅበት ወቅት የኩባንያውን ቀጣይነት በመገምገም ስጋት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን በግልፅ ማመላከትና የኩባንያውን መፍረስ ወይም የአንዳንድ ኦፕሬሽኖችን ስራ ማቆም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የኩባንያውን ቀጣይነት በማሰብ ሂሳቡ የተዘጋጀ መሆኑን የመግለፅ ኃላፊነት አለበት፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ የኩባንያውን የፋይናንሻል ሪፖርት ሂደት የመከታተል ተጨማሪ ኃላፊነት አለበት ፡፡

የኦዲተሮች ኃላፊነት

የእኛ ኃላፊነት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ሆን ተብሎም ሆነ በስህተት ከሚፈፀም ጉልህ ስህተት ነፃ ስለመሆናቸው ምክንያታዊ ማረጋገጫ መስጠትና ይህንኑ አስተያየታችንን በሪፖርታችን መግለፅ ነው፡፡ ምክንያታዊ የሆነ ማረጋገጫ ለመስጠት የሚከናወነው ተግባር በሂሳቡ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ጉልህ ስህተቶችን በሙሉ ፈልጎ ያገኛል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ምክንያቱም ምክንያታዊ ማረጋገጫ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ የማረጋገጥ ሂደት በመሆኑ አለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል የሚከናወነው ኦዲትም ቢሆን ጉልህ ስህተቶችን ሁልጊዜ ፈልጎ የማግኘት ዋስትና ስለማይሰጥ ነው፡፡ ስህተቶች ሆን ተብሎ ወይንም በስህተት የሚፈጸሙና በተናጠል ወይም በድምር ጉልህ ሆነው የሂሳብ መግለጫዎችን መሰረት አድርጎ በሚወሰን ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

የሌሎች ህጋዊ ሁኔታዎች ኦዲት ሪፖርት

በ 2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንቀፅ 1243/2021 በሚያዘው መሰረት የቀረበው የዳሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ የሂሳብ መግለጫዎቹን በተመለከተ ከቀረበው ሪፖርት የተለየ አስተያየት የሌለን መሆኑን እየገለጽን ጠቅላላ ጉባኤው የዳሬክተሮቹን ሪፖርት እንዲያፀድቀው አስተያየታችንን እንሰጣለን፡፡

ታፈሰ፣ ሺሰማ እና አያሌው የኦዲት አገልግሎት የህብረት ሽርክና ማኅበር
የተመሰከረላቸውየሂሳብአዋቂዎች(ዩኬ)
የተፈቀደላቸውኦዲተሮች(ኢትዮጵያ)
የአባይ ባንክ አክስዮን ማህበር የውጭ ኦዲተሮች

አዲስ አበባ
ጥቅምት 20 ቀን 2014 ዓ.ም

ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2021 ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት
የትርፍ ወይም ኪሳራ እና ሌሎች አጠቃላይ ገቢዎች መግለጫ

	ማብራሪያ	ሰኔ 30 2021 ብር'000	ሰኔ 30 2020 ብር'000
የወለድ ገቢ	5	2,462,334	1,507,163
የወለድ ወጪ	6	(807,406)	(567,458)
የተጣራ የወለድ ገቢ		**1,654,928**	**939,705**
ከኮሚሽንና የአገልግሎት ገቢዎች	7	658,734	432,195
ከኮሚሽንና የአገልግሎት ወጭዎች	8	(17,014)	(13,651)
የተጣራ ኮሚሽንና የአገልግሎት ገቢ		**641,720**	**418,544**
ከዉጭ ምንዛሪ ግብይት ላይ የተገኘ የተጣራ ገቢ	9	124,076	67,879
ሌሎች የመደበኛ ሥራ ገቢዎች	10	34,626	35,840
		158,702	**103,719**
አጠቃላይ የመደበኛ ሥራ ገቢዎች		**2,455,350**	**1,461,968**
ለአጠራጣሪ ብድሮች የተያዘ መጠባበቂያ	11	(105,561)	(26,443)
ለሌሎች አጠራጣሪ ተሰበሰባቢዎች የተያዘ መጠባበቂያ	12	(8,889)	(1,511)
የተጣራ የመደበኛ ሥራ ገቢዎች		**2,340,900**	**1,434,014**
የሰራተኛ ወጭዎች	13	(695,407)	451,124
የእርጅና ተቀናሽ	22-23	(64,538)	(46,153)
	21	(141,603)	(108,096)
የሊዝ ወለድ ተከፋይ ወጪ	21	(9,189)	(3,864)
ሌሎች የመደበኛ ሥራ ወጭዎች	14	(277,288)	(184,482)
ከትርፍ ግብር በፊት የተገኘ ትርፍ		**1,152,875**	**640,295**
የትርፍ ግብር	15	(305,726)	(139,092)
ከትርፍ ግብር በኋላ የተገኘ ትርፍ		**847,149**	**501,203**
ያልተከፋፈለ ትርፍ ውስጥ የማይካተቱ:			
ከሰራተኞች የአገልግሎት ጥቅም መጠባበቂያ ዳግም ልኬት	29	9,972	4,032
የአክስዮን ኢንቨስትመንት ወቅታዊ ግምት	18	32,001	22,839
የረጅም ጊዜ የግብር ዕዳ ወጭ ስሌት ማስተካከያ		-	-
		41,973	26,871
ከታክስ በኋላ ያሉ የተጣሩ ሌሎች አጠቃላይ የአመቱ የስሌትገቢዎች		**889,122**	**528,074**
በአክሲዮን ያስገኙት ትርፍ	31	**333.60**	**269.66**

ከገጽ 32-61 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋንኛ አካል ናቸው፡፡

ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2021 ላይ የታየ
የሃብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫ

	ማብራሪያ	ሰኔ 30 2021 ብር ('000)	ሰኔ 30 2020 ብር ('000)
ሀብት			
በእጅና በባንክ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ	16	4,801,551	3,992,344
ለደንበኞች የተሰጠ ብድርና ቅድሚያ ክፍያ(የተጣራ)	17	19,866,631	11,613,432
የአክሲዮን ኢንቨስትመንት	18	176,817	93,010
ሌሎች ፋይናንሺያል ሃብቶች	19	3,750,547	3,800,975
ፋይናንሺያል ያልሆኑ ሃብቶች	20	55,759	37,431
የሊዝ መብት	21	416,155	292,918
ቋሚ ንብረት(የተጣራ)	22	551,423	276,787
ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው ሃብቶች	23	36,535	16,062
ህንፃ ግንባታ ሥራ በሂደት ላይ	24	329,413	65,085
ሊሸጡ በመያዣ የተያዙ ንብረቶች	25	13,758	15,683
ጠቅላላ ሀብት		**29,998,589**	**20,203,730**
ዕዳዎች			
የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ	26	23,913,447	16,098,917
ዓመታዊ የግብር ዕዳዎች	15	305,726	139,092
ፋይናንሺያል ዕዳዎች	27	1,142,140	627,810
የሊዝ ግዴታ	21	138,860	
ፋይናንሺያል ያልሆኑ ዕዳዎች	28	202,813	96,885
ከሠራተኛ ጋር ያሉ ግዴታዎች	29	48,195	30,597
ወደፊት የሚከፈል የትርፍ ግብር	15	19,453	9,742
ጠቅላላ ዕዳዎች		**25,770,634**	**17,114,798**
ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሣቦች			
የተከፈለ ካፒታል	30	2,812,741	2,170,608
ሼር ኘርምየም	30	28,365	28,290
ያልተከፋፈለ ትርፍ	32	600,932	313,106
የሰራተኛ የአገልግሎት ጥቅማጥቅም መጠባበቂያ	29	1,364	(11,503)
ከአክስዮን ኢንቨስትመንት መጠባበቅያ ሂሳብ	18	32,001	22,839
ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ	33	687,116	475,329
በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለብድርና ተሰብሳቢዎት ተጨማሪ መጠባበቂያ	34	65,439	90,262
ጠቅላላ ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሣቦች		**4,227,958**	**3,088,931**
የዕዳዎችና ፣ የባለአክሲዮኖች ገንዘብ ድምር		**29,998,589**	**20,203,730**

ከገጽ 32-61 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋንኛ አካል ናቸው፡፡

የኩባንያው አስተዳዳሪዎች ከገጽ 32-61 ያሉት የሂሳብ መግለጫዎች በቀረቡበት መልኩ እንዲወጡ እ.ኤ.አ ኦክቶበር 29 2021 ፈቅደው አፅድቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ ታደሰ
የቦርድ ሊቀመንበር

የኋላ ገሠሠ
ዋና ሥራ አስፈጻሚ

Tafesse, Shiseema & Ayalew TMS Plus Certified Audit Partnership

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ Accounting and auditing Board of Ethiopia ቁ.6 0118861296 0111541235 ለቦርዱ የቀረበ ኦርጅናል Original Copy Submitted to the board

ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር

እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2021 ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት

በአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል ላይ የታየውን ለውጥ የሚያሳይ መግለጫ

	ማብራሪያ	የተከፈለ ካፒታል ብር '000	ሼር ፕሪምየም ብር '000	ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር '000	ሌሎች መጠባበቂያ ብር '000	ሕጋዊ መጠባበቂያ ብር '000	አጠቃላይ መጠባበቂያ ብር '000	ከአክስዮን ኢንቨስትመንት ብር '000	ድምር ብር '000
እ.ኤ.አ በሀምሌ 1 ቀን 2019 የታየ		1,670,608	28,087	377,565	(15,535)	350,027	34,627	12,073	2,457,452
		-	-	-	-	-	-	-	-
ከአዲስ አክሲዮኖች ሽያጭ የተከፈለ	30	500,000	203	-	-	-	-	-	500,203
በአመቱ የተገኘ ትርፍ	30	-	-	501,203	-	-	-	-	501,203
የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ	32	-	-	(377,565)	-	-	-	-	(377,565)
ለዳይሬክተሮች ቦርድ የትርፍ ድርሻ	32	-	-	(1,350)	-	-	-	-	(1,350)
ከሰራተኛ የአገልግሎት ጥቅም መጠባበቂያ	29	-	-	-	4,032	-	-	-	4,032
የአክሲዮን ኢንቨስትመንት ወቅታዊ ግምገማ	18	-	-	-	-	-	-	10,766	10,766
ወደ ሌሎች መጠባበቂያ የዞረ	32	-	-	(60,031)	-	-	55,635	-	(4,396)
ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ የዞረ	33	-	-	(125,302)	-	125,302	-	-	-
ማስተካከያ (IFRS)	-	-	-	(1,415)	-	-	-	-	(1,415)
እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2020 ላይ የታየ		**2,170,608**	**28,290**	**313,104**	**(11,503)**	**475,329**	**90,262**	**22,839**	**3,088,930**
ጠቅላላ ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሣቦች									
እ.ኤ.አ በሀምሌ 1 ቀን 2020 የታየ		2,170,608	28,290	313,106	(11,503)	475,329	90,262	22,839	3,088,931
ከአዲስ አክሲዮኖች ሽያጭ የተከፈለ	30	642,133	75	-	-	-	-	-	642,208
በአመቱ የተገኘ ትርፍ	30	-	-	847,149	-	-	-	-	847,149
የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ	30	-	-	(313,106)	-	-	-	-	(313,106)
የዳይሬክተሮች የትርፍ ድርሻ	30	-	-	(1,350)	-	-	-	-	(1,350)
ከሰራተኞች የአገልግሎት ጥቅም መጠባበቂያ ዳግም ልኬት	30	-	-	-	9,972	-	-	-	9,972
የአክስዮን ኢንቨስትመንት ወቅታዊ ግምት	30	-	-	-	-	-	-	9,162	9,162
ወደ ሌሎች መጠባበቂያ የዞረ	33	-	-	(25,904)	-	-	(24,823)	-	
ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ የዞረ	33	-	-	(211,787)	-	211,787	-	-	(50,727)
ከሰራተኛ ስንብት ክፍያ ጋር ያሉ ግዴታዎች የስሌት ማስተካከያ (IFRS)		-	-	(7,176)	167	-	-	-	-
እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2021 ላይ የታየ		**2,812,741**	**28,365**	**600,932**	**1,364**	**687,116**	**65,439**	**32,001**	**4,227,958**

ጠቅላላ ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሣቦች

ከገጽ 32 - 61 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋንኛ አካል ናቸው ፡ ፡

Tafesse, Shiferaw & Ayalew
TMS Plus
Certified Audit Partnership

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ
Accounting and auditing Board of Ethiopia
ቁ.6
0118861296
0111541235
ቦርዱ የተረከበ ኦርጅናል ኮፒ
Original Copy Submitted to the Board

ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2021 ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት
የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ

	ማብራሪያ	ሰኔ 30 2021 ብር '000	ሰኔ 30 2020 ብር '000
ከመደበኛ ሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ			
ከመደበኛ ሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ የጥሬ	35	1,242,506	900,286
ለትርፍ ግብር የተከፈለ	15	(139,088)	(181,424)
ከመደበኛ ሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ		**1,103,418**	**718,862**
ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የወጣ			
የኢንቨስትመንት ጭማሪ ግዢ	19	52,160	(11,149)
የአክሲዮን ግዢ ኢንቨስትመንት	18	(51,806)	(22,000)
ለሊዝ የተከፈለ	24	(264,328)	-
ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው ሃብቶች ተከፈለ	23	(23,563)	(459)
የቋሚ ዕቃዎች ግዢ	22	(334,446)	(78,539)
ከቋሚ ዕቃዎች ሽያጭ የተገኘ ገቢ	35	20	-
ከኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የለ የተጣራ		**(621,963)**	**(112,148)**
ከፋይናንሲንግ እንቅስቃሴ			
የትርፍ ድርሻ ተከፈለ	32	(313,106)	(377,565)
ተጨማሪ የተሸጡ አክሲዮኖች	30	642,208	500,203
ለዳይሬክተሮች ቦርድ የትርፍ ድርሻ የተከፈለ	32	(1,350)	-
ከፋይናንሲንግ እንቅስቃሴ የተገኘ		**327,752**	**122,638**
የዓመቱ የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ጭማሪ		**809,207**	**729,352**
በአመቱ መጀመሪያ ላይ የነበረ የገንዘብ	16	3,992,344	3,262,993
የዓመቱ የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ጭማሪ	16	809,207	729,352
በአመቱ መጨረሻ ላይ የታየ የገንዘብ	16	**4,801,551**	**3,992,344**

ከገጽ 32-61 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋንኛ አካል ናቸው፡፡

Tafesse, Shiferaw & Ayalew TMS Plus Certified Audit Partnership

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ Accounting and auditing Board of Ethiopia ቁ.6 0118861296 0111541235 ለቦርዱ የተረከበ ኦርጅናል ኮፒ Original Copy Submitted to the board

ዓባይ ባንክ
Abay Bank

ፍላጎትዎን የሚመጥኑ
በርካታ የብድር አማራጮች

VARIETY OF LOANS
FOR YOUR NEEDS

ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ
Abay - The Trustworthy Bank
Tel +251 11 515 8961, +251 11 554 9735 E-mail: info@abaybank.com.et
Ziquala Complex, Jomo Kenyatta Avenue, ADDIS ABABA, ETHIOPIA
web: www.abaybank.com.et

/abaybanksharecompany

/AbayBank

@AbayBank

/abaybanksharecompany

/In/abaybank